# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራስያዊ ሪፖብሊክ
# (ኢፌዴሪ) ሕገ መንግስት
# መሰረታዊ መርሆዎችና ዋና ዋና መለያ ባህርያት

# Federal Democratic Republic of Ethiopia (FDRE) Constitution-Fundamental Principles and Features

**መግብያ**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራስያዊ ሪፖብሊክ ሕገ መንግስት ፌደራሊዝምን የመሰረተ ሕገ መንግስት ስለሆነ ፌደራሊዝም ማለት ምን ማለት እንደሆነ መገንዘብና የሕገ መንግስቱ መሰረታዊ መርሆዎችንና ባህርያትን መረዳት የኢፌዴሪ ሕገ መንግስትን በተሟላ መንገድ ለመረዳት ከፈተኛ ጠቃሚነት አለው። ሕገ መንግስቱን በሚገባ መንገድ ሳንገነዘብ ድጋፍም ተቃውሞም ማቅረብ ጭፍን ስሜታውነት ከመሆኑም በላይ ለአገራችን የሚፈይደው ነገር የለም። ስለሆነም ስለ ሕገ መንግስቱ መነሻ የሚሆን ግንዛቤ ለመያዝና በአገራችን የሚስተዋሉ ችግሮች ምንጫቸው ሕገ መንግስቱ ነውን? መንግስትስ በሕገ መንግስቱ ምን ያህል እየተመራ ነው? መንግስት ሕገ መንግስቱን ተግባራዊ ለማድረግና ሕገ መንግስቱ ያስሸከመውን አደራና ሃላፊነት ለመተግበርስ ምን ያህል ርቀት ተጉዟል? ዜጎችስ ሕገ መንግስታቸውን ምን ያህል ያውቁታል? ለሕገ መንግስታዊ መብቶቻቸውና ለአገራዊ አንድነታቸው ምን ያህል በጥንካሬና በጋራ ይቆማሉ? የሚሉ ጥያቄዎችን በተገቢ መንገድ ለመመለስ እንድንችል ለመወያያ ሊያገለግል ይችላል ያልኩትን ይህን አጭር ጽሁፍ አቅርቤአለሁ።

ፌደራሊዝም የመንግስት ዓይነት ነው። የፌደራሊዝም መንግስት የአንድ ሉአላዊ አገር ስልጣንን በማእከላዊ መንግስትና በፌደራል ክልሎች የሚያከፋፍል ስርዓት ነው። ስለሆነም ፌደራል የመንግስት አወቃቀር የሚከተሉ አገሮች ሁለት ደረጃ ያለው የመንግስት አወቃቀርን ይመሰርታሉ። ይህም ማለት በማእከል ደረጃና በክልሎች የተከፋፈሉ መንግስታት ማለት ነው። የማእከላዊ መንግስታና የክልል መንግስታት በሕገ መንግስት የተዘረዘረ የየራሳቸው ስልጣን ያላቸው የሕግ አውጪው [ፓርላማ]፣ ህግ አስፈጻሚው [ ሚንስትሮች ም/ቤት]ና የዳኝነት አካል [ፍ/ቤት] መዋቅሮች አሏቸው። ማእከላዊው መንግስት ይህን በሕገ መንግስት የጸደቀ የክልሎች ስልጣንን መቀነስ፣ ማስቀረትና ከዚያ በላይ ስልጣን መጨመር አይችልም። በአብዛኛዎቹ የፌደራሊዝም ስርዓት ተከታይ አገሮች በዓለም አቀፍ ደረጃ እንደ ህጋዊ ሰው ሆኖ አገርን ወክሎ የሚቀርበው አካል የክልሎቹ መንግስታት ሳይሆኑ የማእከላዊው መንግስት ነው።

ክልሎቹ የየራሳቸው ስልጣን ቢኖራቸውም የአንድ አገር አካላት ስለሆኑ እንደ አንድ አገር የሚያስቡና የሚንቀሳቀሱ ስለመሆናቸው ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ አይደለም።

የፌደራሊዝም ተከታይ አገሮች ዜጎች በአንድ ክልል ብቻ እንዲኖሩና እንዲሰሩ የሚያደርግ ገደብ የላቸውም። በየትኛውም ክልሎች የተወለዱ፣ የሚኖሩና የሚሰሩ ሰዎች የአገሪቱ ዜጎች ስለሆኑ በፈለጉበት ግዜ ወደ ፈለጉበት የአገሪቱ ክልል ሄደው መኖርና መስራት ይችላሉ።

ይህ የዜጎች በነጻና ያለምንም ገደብ ወደ ፈለጉት ክልል ተንቀሳቅሰው የመስራትና የመኖር መብት በአገሪቱ እድገት መሰረት የሆነውን የኤኮኖሚ እድገት በፍጥነት እንዲመዘገብ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። ከዚህም በላይ ዜጎች በአንድ ክልል ብቻ ያልታጠረ ዜግነት ያላቸው እንደሆኑ ስለሚያስገነዝብ ክልላቸውን ብቻ ሳይሆን አገራቸውን ለማበልጸግና ለመጠበቅ ጽኑ እምነት እንዲኖራቸው እንዲሁም በሌላ ክልል የሚያጋጥም ችግር የራሳቸው ችግር መሆኑን ተገንዝበው የመፍትሄ አካላት ሆነው የሚንቀሳቀሱ አገራዊ ፍቅርን የሰነቁ ዜጎች እንዲሆኑ ያደርጋል።

የፌደራል መንግስት የክልሎቹ አገራዊ አንድነትን የሚያጠናክሩ ፖሊሲዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣ ተቋሞችን ይገነባል፣ መመርያዎችንና አሰራሮችን ይዘረጋል። ዜጎችን ከጫፍ እስከ ጫፍ ማገናኘት የሚችሉ የስራ ቋንቋዎችን ይለያል ተግባራዊ የሚሆኑበትን መንገድ ይቀይሳል። ማእከላዊ መንግስት ክልሎችን በቀጥታ ማዘዝ ስለሚቸገር ያለውን የኤኮኖሚ አቅም በመጠቀም በክልሎች መተግበር የሚገባውን አንድነትን እንዲያጠናክር አልሞ የነደፈውን ፖሊሲ ማስፈጸም ይችላል። የተነደፈውን ፖሊሲ ለሚተገብሩና ዉጤት ለሚያመዘግቡ ክልሎች ድጎማ ይሰጣል። ካልተገበሩት ድጎማውን ያነሳል።

የክልል መንግስታትና አገሪቱን ለመምራት ሃላፊነት የተጣለበት ገዢ ፓርቲ እነዚህን አገራዊ አንድነትን የሚያጠናክሩ ገመዶችን በጥናት ተመስርተው የመለየት፣ ተግባራዊ የማድረግና የማጠናከር ከፍተኛ ሃላፊነት አለባቸው። የፌደራልና የክልል መንግስታትና ገዢው ፓርቲ ይህን ማድረግ ተስኗቸው የአገሪቱ አንድነት አደጋ ላይ የሚወድቅ ከሆነ ሃላፊነት የጎደላቸውና በታሪክ የሚያስጠይቅ አገራዊ ክህደት እንደፈጸሙ ከመቆጠር አይድኑም።

የፌደራል መንግስት ክልሎች እንደየአገራቸው በተለያዩ ስሞች ይጠራሉ ። ለምሳሌ በካናዳና በአርጀንቲና ክ/ ሃገር፣ በኮሞሮስ አንጂዎን፣ በአሜሪካ፣ በአውስትርያና በጀርመን ስቴት፣ በኔፓል ዞን፣ በስዊዘርላንድ ካንቶን፣ በዩናይትድ አረብ ኢማሬትስ ኢማሬትስና በኢትዮጵያ ክልል እየተባሉ ይጠራሉ።

ፌደራሊዝምና አሃዱአዊ የመንግስት ስርዓቶች መሰረታዊ የሚባሉ ልዩነቶች አሏቸው። አሃዱአዊ የመንግስት አወቃቀር ከፌደራላዊ የመንግስት አወቃቀር የሚለይባቸውን አንዳንድ ነጥቦችን ለመጥቀስ ሀ/ አሃዱአዊ የመንግስት አወቃቀር አንድን ሉአላዊ የስልጣን እርከን በማእከል ደረጃ አቋቁሞ የመንግስት መዋቅሩን በሚመቸው መንገድ እስከ ታች ድረስ በሰንሰለት ዘርግቶ የሚመራ መንግስትን ያቋቁማል። ለ/ አሃዱአዊ መንግስት እስከ ታች ድረስ ያደራጀውን መዋቅር የፈለገውን የስልጣን መጠንና ዓይነት መስጠት ይችላል። ሳይፈልግ ሲቀር ደግሞ መዋቅሩን ማፍረስና መቀየር እንዲሁም በየደረጃው ያሉትን አካላት ስልጣናቸውን መቀነስ ወይንም ማንሳት ይችላል። በአጼ ሃይለስላሴና በደርግ መንግስት ዘመን የነበሩት የኢትዮጵያ የመንግስታት ዓይነት የአሃዱአዊ ስርዓት ሁነኛ ምሳሌዎች ሊሆን ይችላሉ።

ፌደራላዊ ስርዓት አዲስና በመስፋፋት ላይ ያለ የመንግስት ዓይነት ነው። እስከ አሁን ድረስ በዓለማችን ውስጥ ካሉ 195 አገሮች 25ቱ የፌደራሊዝም ስርዓት ተከታይ ሆነዋል። ፌደራሊዝምን የሚከተሉ አገሮች አንዳንዶቹ ፕረዚደንታዊ ስርዓት ሲከተሉ ሌሎቹ ደግሞ ፓርላሜንታዊ ስርዓትን ይከተላሉ። አንዳንዶቹ አገሮች ሁለት ወይንም ሶስት ክልሎች ብቻ ሲኖሯቸው ሌሎቹ ደግሞ እስከ አርባ ወይንም ሃምሳ የሚደርሱ ክልሎች አሏቸው።

የእነዚህ የፌደራል መንግስት ተከታይ አገሮች ሕገ መንግስት ለክልሎቹና ለሶስቱ የመንግስት አካላት የሚሰጠው ስልጣን፣ ክልሎቻቸውን የሚያካልሉበት መንገድ ወዘተ የተለያየ ነው። በዓለማችን ያሉ ፌደራሊዝም ተከታይ አገሮች ክልሎቻቸው፣ የክልሎቻቸው መጠርያ ስምና የክልሎቻቸው ብዛት ቀጥሎ ከቀረበው ዝርዝር መረዳት ይቻላል።

| **አገር** | **ባንዲራ** | **የክልሎች ብዛት** | **የክልል መጠርያ ስም** |
|---|---|---|---|
| አርጀንቲና |  | 23 | ፕሮቪንስና አንድ ራስ ገዝ ከተማ [ ቦኔስ አይረስ] |
| አውስትራልያ |  | 6 | ስቴትና ሁለት ክልሎች |
| አውስትርያ |  | 9 | ስቴትስ |
| ቤልጅም |  | 3 | ክልሎችና የቋንቋ ከባቢዎች |
| ቦዝንያ ሄርዘአቨንያ |  | 2 | ኢንቲቲና አንድ ዲስትሪክት |
| ብራዚል |  | 26 | ስቴትና ፌደራል ዲስትሪክት |
| ካናዳ |  | 10 | ፕሮ ቪንቾ ና 3 አከባቢዎ ች |
| ኮሞሮስ |  | 4 | አንጁዋን፣ ግራንደ፣ ግራንደ ኮመሬ |
| ኢትዮጵያ |  | 9 | ክልሎችና ሁለት ቻርተርድ ከተሞች |
| ጀርመን |  | 16 | ስቴትስ |
| ህንድ |  | 29 | ስቴትስና 7 ዩንየን ተሪተሪስ |
| ኢራቅ |  | 18 | ጎቨርኖሬትስና አንድ ክልል፣ ኩርዲስታን |
| ማላይሲያ |  | 13 | ስቴትትና 3 ፌደራል ተሪቶሪስ |
| ሜክሲኮ |  | 31 | ስቴትና 1 ፌደራል ዲስትሪክት፣ ሜክሲኮ ከተማ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፌደሬትድ ስቴትስ ኦፍ ሚክሮኔስያ |  | 4 | ቹክ፣ ኮስራይ፣ ፖህንፐይ፣ያፐ |
| ኔፓል |  | 14 | ዞኖች |
| ናይጀርያ |  | 36 | ስቴቶችና አንድ ፌደራል ቴሪቶ ሪ፣ ፌደራልካፒታል ቴሪቶሪ |
| ፓኪስታን |  | 4 | ፐሮቪንስ፣፣2 አውቶኖሞስ ኤርያ፣ 2 ተሪቶሪስ |
| ሩስያ |  | 46 | ኦብላስት፣ 22 ሪፓብሊክስ፣9 ክሪያስ፣4 አውቶኖሞስ ኦክራግስ፣3 ፌደራል ከተሞች፣ 1 አውቶኖሞስ ኦብላስት |
| ሰይንት ኪትስና ነቪስ |  | 2 | ሰይንት ኪትስና ነቪስ |
| ደቡብ ሱዳን |  | 10 | ስቴትስ |
| ስዊዘርላንድ |  | 26 | ካንቶንስ |
| ዩናይትድ አረብ ኤመሬትስ |  | 7 | ኤሜሬትስ |
| ዩናይት ስቴትስ |  | 50 | ስቴትስ፣ 1 ኢንኮርፖሬትድ ቴሪተሪ፣1 ፌደራል ዲስትሪክት፡ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምብያ |
| ቬኑዝላ |  | 23 | ስቴትስ፣ 1 ካፒታል ዲስትሪክት፣1 ፌደራል ዲፔንደንሲ |

ሁሉም የፌደራሊዝም ተከታይ አገሮች የየራሳቸው የሆነ የአከላለል ስርዓት፣ የስልጣን ክፍፍልና የቋንቋ አጠቃቀም ዘዴዎችን ይከተላሉ። የስዊዘርላንድ የፌደራሊዝም ስርዓትን እንደ አብነት ወስደን እንመልከተው።

**ስዊዘርላንድ [ስዊስ]**



ከ1815 ዓ/ም ጀምራ በጦርነት ገብታ የማታውቀውና በ2002 ወደ ተባበሩት መንግስታት የተቀላቀለችው ስዊዘርላንድ በ1848ዓም ፌደራላዊ የመንግስት ስርዓትን የመሰረተች አገር ናት።ስዊዘርላንድ በጣልያን፣ ፈረንሳይ፣ጀርመን፣አውስትሪያና ሊቸንስቴን የምትዋሰን እንደ

ኢትዮጵያ የባህር በር የሌላት በመሬት የተከበበች አውሮፓዊት አገር ስትሆን የህዝብ ብዛቷም 8,327,126 ነው [2015] ። ዋና ከተማዋ የፌደራል መንግስት መቀመጫ የሆነችው ከተማ በርን ትባላለች። ከዚህ በተጨማሪ ዙሪክ፣ጀኔቫ፣ ጀርመንና ፍሬንች የተባሉ በኑሮ ጥራታቸው ከፊት የሚሰለፉ ትላልቅ ከተሞች አሏት። ዙሪክ አንድ ተኩል ሚልዮን ህዝብ የሚኖርባት ከተማ ስትሆን በውስጧ 150, 000 ካምፓኒዎችን አቅፋለች።

በጦርነት ጣልቃ አለመግባትና በገለልተኛነት የምትታወቀው ስዊዘርላንድ ፌደራሊዝምን የምትከተል አገር ስለሆነች መንግስቷ በማእከላዊ መንግስትና በ26 ካንቶንስ እየተባሉ በሚጠሩ ክልሎች የተዋቀረ ነው። ስዊዘርላንድ ጀርመን፣ ፈረንሳይ፣ጣልያንና ሮማንያ በሚባሉ አራት ዋነኛ በቋንቋና በባህል የተከፋፈሉ ሪጅኖች የተከፋፈለች አገር ስትሆን አራት መደበኛ የስራ ቋንቋዎችም እንዲኖራት በሕገ መንግስት አንቀጽ 70 ደንግጋለች። እነዚህም ጣልያንኛ [8.1%], ሮማንኛ [0.5%], ጀርመንኛ [63.5%]ና ፈረንሳይኛ [22.5%] ናቸው። የፌደራል መንግስት በመደበኛ ቋንቋዎቹ እንዲያስተናግድ ግዴታ ያለው ሲሆን በፌደራል ፓርላማ ደግሞ ከ እና ወደ ጀርመንኛ፣ፈረንሳይኛና ጣልያንኛ የመተርጎም አገልግሎት ይሰጣል።

ስዊዘርላንድ እንደ ኢትዮጵያ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ህዝቦችን ያቀፈች ስለሆነች የክልል/ካንቶን መንግስታቷ የተዋቀሩት የህዝቦቿ በየቋንቋቸው አሰፋፈርን መሰረት ያደረገ ነው። እነዚህ ክልሎች/ ካንቶንስ ደግሞ የራሳቸው መደበኛ ቋንቋቸው እንዲወስኑ በአንቀጽ 70 [2] ሕገ መንግስታዊ መብትን ተጎናጽፏል። የካንቶኖቹ የህዝብ ብዛት እጅግ የተለያየ ነው። ለምሳሌ አፐርሀንድ ኢንተርሆደን የተባለች ካንቶን 15,000 ህዝብ ሲኖራት ዙሪክ ደግሞ 1,253,500 የህዝብ ብዛት አላት። የካንቶኖቹ የቆዳ ስፋትም የተለያየ ነው ያነሰችው ካንቶን/ ክልል 37 ስኬር ኪ/ሜ [ቤሰልስታዲት] ስትሆን ትልቋ ካንቶን/ ክልል ደግሞ 7,105 ስኬር ኪ/ሜ [ግራውበንደን] ናት።

የስዊስ ፓርላማ ሁለት ም/ቤቶች አሉት። አንደኛው ኮንስል ኦፍ ስቴትስ ሲባል ከያንዳንዱ ክልል/ካንቶን የተወከሉ ሁለት ሁለት ተወካዮች ከግማሽ ካንቶን ደግሞ አንድ አንድ በተወከሉ በድምር 46 አባላትን ያቀፈ ነው። ሁለተኛው ም/ቤት ናሽናል ኮንስል የሚባል ሲሆን ባለው ህዝብ ብዛት መሰረት በተመጣጠነ የውክልና ቁጥር ባላቸው 200 አባላት የቆመ ነው። ሁለቱም ም/ቤቶች ለ4 ዓመታት ብቻ ያገለግላሉ።

ዜጎች በሪፈረንደም ፓርላማ ያጸደቀውን ሕግ እስከማውደቅና ሕገ መንግስታቸውን እስከ ማሻሻል ድረስ የሚደርስ መብት አላቸው። የስዊስ መንግስት የተዋቀረው በአገሪቱ ውስጥ ባሉ 4 ዋና ዋና ፓርቲዎች ጥምረት ነው።

የስዊስ ዜጎች በቡድን ተደራጅተው ፌደራል ሪፈረንደምን በመጥራት በ100 ቀናት ውስጥ የ50, 000 ፊርማዎችን ማሰባሰብ ከቻሉ በፓርላማ የተላለፈውን ህግ ማስቀየር ይችላሉ። 8 ካንቶኖች ሕገ መንግስታዊ ሪፈረንደም በመጥራትም ደግሞ በፌደራል መንግስት የተላለፈውን ህግ ውድቅ ማድረግ ይችላሉ።

ካንቶኖቹ ሌሎች አገሮች ጋር ካሉ ክልሎች ሲነጻጸሩ ቀዋሚ ሕገ መንግስታዊ ማንነትና ከፍተኛ ደረጃ ያለው ነጻነት አላቸው ማለት ይቻላል። በፌደራል ሕገ መንግስት ደግሞ እያንዳንዳቸው ካንቶኖች እኩል ደረጃ አላቸው። እያንዳንዱ ካንቶን የራሱ የሆነ ሕገ መንግስት፣ፓርላማ፣ መንግስትና ፍ/ቤት አለው። ይሁን እንጂ በካንቶኖቹ መካከል በህዝብ ብዛትና በጂኦግራፊ ስፋት ከፍተኛ ልዩነት አለ። እነዚህ ካንቶኖች በድምር 2,485 ማዛጋጃ ቤቶች አሏቸው። ስዊስ በካንቶኖች ብትለያይም ህዝቦቿ በአገር ጉዳይ በአንድ ደወል የሚንቀሳቀሱ ጠንካራ አገራዊ አንድነት ያላቸው ዜጎች እንደሆኑ ይነገርላቸዋል።

የስዊስ አቀማመጥና የመስተዳድር ክልሎች

ስዊስ አውሮፓዊት ከተማ ነች

ስዊስ 26 ካንቶኖች አሏት






**ካንቶኖች፣ ዋና ከተማቸው፣ የህዝብ ብዛታቸውና ዋና ቋንቋቸው**

| ካንቶን | ዋና ከተማ | የህዝብ ብዛት | ዋና ቋንቋ |
|---|---|---|---|
| ዙሪክ | ዙሪክ | 1,463,459 | ጀርመንኛ |
| በርን | በርን | 1,017,483 | ጀርመንኛና ፈረንሳይኛ |

| ካንቶን | ዋና ከተማ | የህዝብ ብዛት | ዋና ቋንቋ |
|---|---|---|---|
| ስዊዘርላንድ | በርን | 8,327,126 | ጀርመንኛ፣ፈረንሳይኛ፣ ጣልያንኛ፣ ሮማንኛ |

## የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት መሰረታዊ መርሆዎችና ባህርያት

ክፍ ብለን ፌደራሊዝም ማለት ምን ማለት እንደሆነና አንድ ፌደራሊዝም ተከታይ አገር [ስዊዘርላንድን] እንደ አብነት በመውሰድ ለማየት ሞክረናል። ቀጥለን የኢትዮጵያ ፌደራል ሕገ መንግስት መሰረታዊ መርሆዎችንና ባህርያትን በአጭሩ እንመለከት።

### መሰረታዊ መርሆዎች [Fundamental Principles]

መሰረታዊ መርህ ማለት አንኳርና ዋናው አንድ አገር የምትመራበት መመርያ ማለት ነው። ሌሎች መመርያዎችና ሃቆች የሚመነጩት ከዚህ መሰረታዊ መርህ ነው። የኢፌድሪ ሕገ መንግስትም የተለያዩ መርሆዎችን አስፍሯል። ቀጥለን እንመልከታቸው።

---

### ሀ/ የኢፌድሪ ህገ መንግስት መሰረታዊ መርሆዎች [Principles of FDRE Constitution]

የኢፌድሪ ህገመንግስት መሰረታዊ መርሆቹን በመግብያውና በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የተዘረዘሩት አንቀጾች 8፣ 9፣ 10ና 12 ውስጥ በዝርዝር አስፍሯል። እነዚህን አንድ በአንድ ለመቃኘት እንሞክር።

### መ ግ ቢ ያ [Preamble]

እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች፡በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፤ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን፣ የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ በነጻ ፍላጐታችን፣ በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን በመነሳት፤ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ፣ የግለሰብና የብሔር/ብሔረሰብ መሰረታዊ መብቶች መከበራቸው፣ የጾታ እኩልነት መረጋገጡ፣ ባሕሎችና ሃይማኖቶች ካለአንዳች ልዩነት እንዲራመዱ የማድረጉ አስፈላጊነት ጽኑ እምነታችን በመሆኑ፤ኢትዮጵያ ሀገራችን የየራሳችን አኩሪ ባሕል ያለን፣ የየራሳችን መልክዓ ምድር አሰፋፈር የነበረንና ያለን፣ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የኖርንባትና የምንኖርባት ሀገር በመሆንዋ፤ ያፈራነው የጋራ ጥቅምና አመለካከት አለን ብለን ስለምናምን፤መጪው የጋራ ዕድላችን መመስረት ያለበት ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅማችንን በማሳደግ ላይ መሆኑን በመቀበል፤ ጥቅማችንን፣ መብታችንና ነጻነታችንን በጋራ እና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመገንባቱን አስፈላጊነት በማመን፤ በትግላችንና በከፈልነው መስዋዕትነት የተገኘውን ዴሞክራሲና ሰላም ዘላቂነቱንለማረጋገጥ፤ይህ ሕገ መንግሥት ከዚህ በላይ ለገለጽናቸው ዓላማዎችና እምነቶች ማሰሪያ እንዲሆነን እንዲወክሉን መርጠን በላክናቸው ተወካዮቻችን አማካይነት በሕገ መንግሥት ጉባኤ ዛሬ ኅዳር 29 ቀን 1987 አጽድቀነዋል፡፡ ይላል።

ይህ ሕገ መንግስት በመግብያው ላይ ለአገሪቱ መመርያ ይሆናሉ ያላቸውን የሚከተልቱን አንኳር መሰረታዊ መርሆዎችና ባህርያትን አስፍሯል። እነዚህም፡—

- ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣
- ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን፣
- የራሳችንን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ በነጻ ፍላጐታችን እንዲገነባ፣
- በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሰረተ
- አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ ለመገንባት ፤
- የግለሰብና የብሔር/ብሔረሰብ መሰረታዊ መብቶች መከበራቸው ለማረጋገጥ፣
- የጾታ እኩልነት ለማረጋገጥ፣
- ባሕሎችና ሃይማኖቶች ካለአንዳች ልዩነት እንዲራመዱ ለማድረግ
- ኢትዮጵያ ሀገራችን የየራሳችን አኩሪ ባሕል ያለን፣ የየራሳችን መልክዓ ምድር አሰፋፈር የነበረንና ያለን፣ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የኖርንባትና የምንኖርባት ሀገር በመሆንዋ፤ መጪው የጋራ ዕድላችን መመስረት ያለበት ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅማችንን በማሳደግ ላይ መሆኑን በመቀበል፤ ጥቅማችንን፣ መብታችንና ነጻነታችንን በጋራ እና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ
- አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመገንባቱን አስፈላጊነት በማመን፤
- ዴሞክራሲና ሰላም በዘላቂነት ማረጋገጥ ናቸው።

**ከመግብያው የምንረዳው መሰረታዊ ነገር ቢኖር ሕገ መንግስቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላምና ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ የሕግ የበላይነት፣የግለሰቦች፣ የሃይማኖቶች፣የጾታና የብሄርና ብሄረሰብ መብቶች የተረጋገጠበት አንድ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ በጋራ መገንባትን እንደዋነኛ መርህና ባህርይ አንግቦ መነሳቱን ነው።**

ሕገ መንግስቱ ከመግብያው በተጨማሪ በሚከተሉት አንቀጾች መሰረታዊ መርሆዎችን ዘርዝሯል።

**አንቀጽ 8: የሕዝብ ሉዓላዊነት [Sovereignty]** የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው፡፡

**አንቀጽ 9: የሕገ መንግሥት የበላይነት [constitution is the supreme Law]**

ሕገ መንግሥቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር፣እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡ ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው፣ ሕገ መንግሥቱን የማስከበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በዚህ ሕገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው ካለ በኋላ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችም የሀገሪቱ ሕግ አካል ናቸው፡፡ ይላል።

**አንቀጽ 10: የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች [Human and Democratic Rights]**

ሰብዓዊ መብቶችና ነጻነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ፣ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው፡፡ የዜጐች እና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው፣ ሕገ መንግሥቱን የማስከበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡ በዚህ ሕገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ እንደሆነም አስፍሯል። በማከታተል ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕግ አካል ናቸው፡፡ ይህ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ድንጋጌንም [ዩኒቨርሳል ዲክላረሽን ኦፍ ሂማን ራትስ] ያካትታል ማለት ነው።

**አንቀጽ 11: የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት [Separation of State and Religion]**

መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፡፡ መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም፡፡ መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡

**አንቀጽ 12: የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት [Conduct and Accountability Of Government]**

የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡ ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡ሕዝብ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ለማንሳት ይችላል፡፡ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

**ለ/ የኢፌድሪ ህገ መንግስት ዋና መለያ ባህርያት [Features of FDRE Constitution]**

የኢፌድሪ ሕገ መንግስት መሰረታዊ መርሆዎቹን ብቻ ሳይሆን ያሰፈራቸውን ባህርያቶች መረዳትም ሕገ መንግስቱን በተሟላ መንገድ ለመረዳት ስለሚያስችለን ቀጥለን የሕገ መንግስቱን ባህርያት ለማየት እንሞክራለን።

**ምዕራፍ ሦስት: መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶች**

የኢፌድሪ ህገ መንግስት በ40 አንቀጾች የተዘረዘሩ መሰረታዊ መብቶችና ነጻነቶችን አስፍሯል። ከነዚህ ውስጥ ይህ ጽሁፉ ትኩረት እንዲሰጣቸው በፈለጋቸው ላይ እናተኩራለን።

**አንቀጽ 39 የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መብት [Rights of Nations, Nationalities, and Peoples]**

- ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው፡፡
- ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመጻፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባሕሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው፡፡
- ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት ብሔሩ፣ ብሔረሰቡ፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በክልልና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል፡፡ የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት ከሥራ ላይ የሚውልበት አገባብ ሲገልጽ ደግሞ እንዲህ ይላል።

ሀ/ የመገንጠል ጥያቄ በብሔር፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ የሕግ አውጪ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ የድምጽ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፤

ለ/ የፌዴራሉ መንግሥት የብሔር፣ የብሔረሰቡ ወይም የሕዝቡ ምክር ቤት ውሳኔ በደረሰው በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው ብሔር፣ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፤

ሐ/ የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝበ ውሳኔው በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፤

መ/ የፌዴራሉ መንግሥት መገንጠሉን ለመረጠው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ምክር ቤት ሥልጣኑን ሲያስረክብ፤

ሠ/ በሕግ በሚወሰነው መሠረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው፡፡ ይላል፡፡

በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ «ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ» ማለት ከዚህ ቀጥሎ የተገለጸውን ባህርይ የሚያሳይ ማኅበረሰብ ነው፡፡ ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባሕል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው፡፡

## አንቀጽ 45 ሥርዓተ መንግሥት [Form of Government]

- የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሥርዓተ መንግሥት ፓርላሜንታዊ ነው፡፡

## አንቀጽ 46 የፌዴራል ክልሎች [States of the Federation]

- የፌዴራሉ መንግሥት በክልሎች የተዋቀረ ነው፡፡
- ክልሎች የሚዋቀሩት በሕዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ የማንነት እና ፈቃድ ላይ በመመስረት ነው፡፡

## አንቀጽ 47 የፌዴራል መንግሥት አባላት [Member States of the Federal Democratic Republic]

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባላት የሚከተሉት ናቸው፡፡

1- የትግራይ ክልል

2- የአፋር ክልል
3- የአማራ ክልል
4- የኦሮሚያ ክልል
5- የሱማሌ ክልል
6- የቤንሻንጉል/ጉሙዝ ክልል
7- የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል
8- የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል
9- የሐረሪ ሕዝብ ክልል

በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱት ክልሎች ውስጥ የተካተቱ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በማንኛውም ጊዜ የየራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት አላቸው፡፡ የማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ክልል የመመስረት መብት ሥራ ላይ የሚውለው፤

ሀ/ የክልል መመስረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥና ጥያቄው በጽሑፍ ለክልሉ ምክር ቤት ሲቀርብ፤

ለ/ ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤት ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፤

ሐ/ ክልል የመመስረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ ሕዝበ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፤

መ/ የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣኑን ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሲያስረክብ፤

ሠ/ በሕዝበ ውሳኔ የሚፈጠረው አዲስ ክልል ጥያቄ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል ሲሆን ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባላት እኩል መብትና ሥልጣን አላቸው፡፡

**አንቀጽ 78 ስለ ነጻ የዳኝነት አካል [Independence of the Judiciary]**

- ነጻ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል፡፡
- የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ የዳኝነት አካል የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሀገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲደራጅ በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሊወስን ይችላል፡፡ ጉዳዩ በዚህ አኳኋን ካልተወሰነ የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ለክልል ፍርድ ቤቶች ተሰጥቷል፡፡
- ክልሎች፣ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች፣ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ይኖራቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይዋሰናል፡፡
- የዳኝነት ሥልጣንን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጭ የሚያደርግ፣ በሕግ የተደነገገን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ፍርድ ቤት ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም፡፡መሰረት የሃይማኖትና የባሕል ፍርድ ቤቶችን ሊያቋቁሙ ወይም እውቅና ሊሰጡ ይችላላላለላሉ፡፡ ይህ ሕግ መንግሥት

ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ ሃይማኖቶችና የባሕል ፍርድ ቤቶች በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት እውቅና አግኝተው ይደራጃሉ፡፡

**አንቀጽ 82 የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አወቃቀር [Structure of the Council of Constitutional Inquiry]**

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል፡፡
የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አሥራ አንድ አባላት ይኖሩታል፡፡አባላቱም የሚከተሉት ናቸው፣

ሀ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ሰብሳቢ፤

ለ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ሰብሳቢ፤

ሐ/ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅራቢነት በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚሾሙ በሙያ ብቃታቸውና በሥነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች፤

መ/ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል የሚወክላቸው ሦስት ሰዎች፡፡

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሥራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ የሚያስችለው መዋቅር ሊዘረጋ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 83 ሕገ መንግሥቱን ስለመተርጐም [Interpretation of the Constitution]**

- የሕገ መንግሥታዊ ክርክር ጉዳይ ሲነሳ በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ውሳኔ ያገኛል፡፡
- የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ በሚያቀርብለት ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ በሠላሣ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡

**አንቀጽ 84 የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሥልጣንና ተግባር [Powers and Functions of the Council of Constitutional Inquiry]**

- የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ በሚያደርገው ማጣራት መሰረት ሕገ መንግሥቱ መተርጐም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል፡፡
- በፌዴራሉ መንግሥትም ሆነ በክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ ሕጐች ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳና ጉዳዩም በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለ ጉዳዩ ሲቀርብለት መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
- በፍርድ ቤቶች የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ፣
- ሀ/ ሕገ መንግሥቱን መተርጐም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይመልሳል፤ በአጣሪ ጉባኤው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለጉዳይ ቅሬታውን ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
- ለ/ የትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል፡፡ የሚመራበትን ሥነ ሥርዓት አርቅቆ ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 85 ዓላማዎች [Objectives]**

- ማንኛውም የመንግሥት አካል ሕገ መንግሥቱን፣ ሌሎች ሕጐችንና ፖሊሲዎችን ሥራ ላይ ሲያውል በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት መርሆዎችና ዓላማዎች ላይ መመስረት አለበት፡፡
- በዚህ ምዕራፍ ውስጥ «መንግሥት» ማለት እንደየሁኔታው የፌዴራል መንግሥት ወይም የክልል መስተዳድሮች ማለት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 86 የውጭ ግንኙነት መርሆዎች [Principles for External Relations]**

- የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅና የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማራመድ
- የመንግሥታትን ሉዓላዊነትና እኩልነት ማክበር፣ በሌሎች ሀገሮች ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ አለመግባት፡፡
- የሀገሪቱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በጋራ ጥቅምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ስምምነቶች የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡
- የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚያስከብሩና የሕዝቦቿን ጥቅም የማይጻረሩ ዓለም አቀፍ ሕጐችና ስምምነቶችን ማክበር፡
- ከጐረቤት ሀገሮችና ከሌሎችም የአፍሪካ ሀገሮች ጋር በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ኅብረትና የሕዝቦች ወንድማማችነትን ማጐልበት፡፡
- በሀገሮች መካከል የሚነሱ ግጭቶች ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ጥረት ማድረግ፡፡

**አንቀጽ 87 የመከላከያ መርሆዎች [Principles for National Defence]**

- የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦች እና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋጽኦ ያካተተ ይሆናል፡፡
- የመከላከያ ሚኒስትር ሆኖ የሚሾመው ሲቪል ይሆናል፡፡
- የመከላከያ ሠራዊት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ከመጠበቅ በተጨማሪ በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፡፡
- የመከላከያ ሠራዊቱ በማናቸውም ጊዜ ለሕገ መንግሥቱ ተገዢ ይሆናል፡፡
- የመከላከያ ሠራዊቱ ተግባሩን ከፖለቲካ ድርጅቶች ወገናዊነት ነጻ በሆነ አኳኋኑን ያከናውናል፡፡

**አንቀጽ 88 ፖለቲካ ነክ ዓላማዎች [Political Objectives]**

- መንግሥት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመሥረት ሕዝቡ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡
- መንግሥት የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችን፣ የሕዝቦችን ማንነት የማክበርና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው እኩልነት፣ አንድነትና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 89 ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች [Economic Objectives]

- *መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያውያን የሀገሪቱ የተጠራቀመ እውቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት፡፡*
- *መንግሥት የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት፡፡*
- *የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጐጂው እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ፡፡*
- *በእድገት ወደኋላ ለቀሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መንግሥት ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፡፡*
- *መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ሥም በይዞታው ሥር በማድረግ ለሕዝቡ የጋራ ጥቅምና እድገት እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡*
- *የሀገር ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት መንግሥት ሕዝቡን በየደረጃው ማሳተፍ አለበት፡፡ የሕዝብንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት፡፡*
- *መንግሥት በሀገር ኢኮኖሚያዊና ማኀበራዊ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት፡፡*
- *መንግሥት የሠራተኛውን ሕዝብ ጤንነት፣ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት፡፡*

## አንቀጽ 90 ማኅበራዊ ነክ ዓላማዎች [Social Objectives]

- *የሀየሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንዐህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማኀበራዊ ዋስትና እንዲኖረው ይደረጋል፡፡*
- *ትምህርት በማናቸውም ረገድ ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶች እና ከባህላዊ ተፅእኖዎች ነጻ በሆነ መንገድ መካሔድ አለበት፡፡*

## አንቀጽ 91 ባሕል ነክ ዓላማዎች [Cultural Objectives]

- *መንግሥት መሰረታዊ መብቶችንና ሰብዓዊ ክብርን፣ ዴሞክራሲንና ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑ ባሕሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጐለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት፡፡ የሀገር የተፈጥሮ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግሥትና የሁሉም ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው፡፡መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነጥበብን፣ ሳይንስንና ቴኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት፡፡*

## አንቀጽ 92 የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች [Environmental Objectives]

*መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንጹሕና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት አለበት፡፡ ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የሚያናጋ መሆን አለበት፡፡*

የሕዝብን የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚመለከተው ሕዝብ ሁሉ ሐሳቡን እንዲገልጽ መደረግ አለበት፡፡

- መንግሥትና ዜጎች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ እንዳለባቸው አስፍሯል፡፡